**የተቋሙ ታርካዊ ዳራ**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት የሥራ አመራር ማሰልጠኛ ተቋም በ1991 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር15/1991 ራሱን ችሎ ሲቋቋም ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር እና ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነበር፡፡**ተቋሙ በ1991 ዓ.ም ሲቋቋም የሚከተሉት ተግባር እና ሀላፊነቶች ነበሩት፡-**

❖ በክልሉ የሚካሄደውን ስልጠና ስርዓት ባለው መንገድ ለማካሄድና የክልሉን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የስልጠና አሰጣጥን ለማስፈን የሚያስችል ዘዴ ለመቀየስ፣

❖ በክልሉ በየደረጃው ተሰማርቶ የሚገኘውን የሰው ሀይል የስራ አመራር ብቃቱን እንዲያጎለብት አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎች ለመስጠት የሚሉ አላማዎችን ይዞ ተቋሙ ሀምሌ 27/1991 ዓ.ም በተካሄደው የክልሉ ም/ቤት 7ኛ መደበኛ ጉባኤ ሲቋቋም በአዋጅ ስልጣን ተሰጥቶት በበጀት፣ በሰው ሀይል እና በማቴሪያል ተደራጅቶ በይፋ ስራ የጀመርው ነሀሴ 1/1992 ዓ.ም ሲሆን ያለው የሰው ሀይል ብዛት አንድ ተሾሚ እና 23 ሰራተኞች ነበሩት፡፡ ተቋሙ የራሱ የሆነ ህንጻና ግቢ ከመጀመሪያው ጀምሮ በተቋሙ ደረጃ ለስልጠና ማዕከል ያልተገነባ በመሆኑ ምክንያት ተቋሙ የመቀበል አቅሙ 80 ሰልጣኞችን ብቻ እንዲያስተናግድ መገደቡ ዋናው ችግር ነበር፡፡ ተቋሙ መስከረም 1995 ዓ.ም በአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ሥር እንዲተዳደር ተደረገ፡፡ ተቋሙ በአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ሥር እንዲተዳደር ሲወሰን በተቋሙና በአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ መሀከል መኖር ስለሚገባዉ ግንኙነትና የተቋሙ ተግባርና ኃላፊነትን የመተዳደሪያ መዋቅር የበጀትና ፋይናንስ አጠቃቀም ግልፅ ሆኖ የተቀመጠ አልነበረም፡፡ ተቋሙ መጀመርያ በአዋጅ ሲቋቋም በቦርድ እንደሚተዳደር የተገለፀ ቢሆንም የቦርድ አባላቱ ተዋፅኦና ብዛት በዉል የማይታወቅ በመሆኑ ለተቋሙ መዳከም ተጨማሪ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ቦርዱ ተቋቁሞ የቦርድ ስልጣን፣ተግባርና ኃላፊነት እንደዚሁም የተቋሙ ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት በተዋረድ በአዋጅ ቢጠቀስም ከላይ እንደተጠቀሰዉ ቦርዱ በአካል ባለመቋቋሙ ተቋሙ የስልጠና፣ የምክር እና ጥናትና ምርምር አገልግሎት በመስጠት ከሚያገኘዉ ገቢ መጠቀም አልቻለም ነበረ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ1997 ዓ.ም በፊት ሲጠቀምበት የነበረውን ቦታ ለቆ(የአሁኑ የክልሉ ህጻናት እና ሴቶች ጉዳይ ቢሮ የሚገኝበት አጥር ግቢ ውስጥ) አሁን ካለበት አምባ አምስት ለፖሊስ ማሰልጠኛ ከተገነባው ህንጻ ውስጥ እንዲገባ ተደርገ፡፡ ይህም ህንጻ በወቅቱ ለስልጠና ማዕከል ተብሎ ስላልተገነባ ምቹ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ የውሀ፣የስልክ መስመር፣የመብራት፣የሻወር እና የሽንት ቤት የኢንስታሌሽን መስመር ዝረጋት ብልሽት ችግሮች ከመኖሩም በላይ ተቋሙን ሥራ ሊያሰራ የሚያስችል ድርጅታዊ መዋቅር ባለመኖሩ ምክንያት ብቃት ያላቸውን

አሰልጣኞች እና አማካሪ ባለሙያዎችን መቅጠር ያልቻለበት ሁኔታ ነበር፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ ድጋፍ ሰጪ የሚበዛበት በአንፃሩ ዓላማ አስፈፃሚ ባለሙያ የሚያንስበት ነበር፡፡ በመሆኑም ተቋሙ ያሉበትን ችግሮች ለመቅረፍ እና የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት እንዲያስችለው ለማድረግ በ2002 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 89/2002 እንደገና እንዲቋቋም እና እንዲደራጅ ተድርጓል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡፡ በየደረጃዉ የሚገኙ የክልል የመንግስት አካላት የሥራ አመራር ብቃት እንዲጎለብት አስፈላጊ የሆኑትን፤የሥራ አመራር ስልጠናዎች፤ምርምሮችና የምክር አገልግሎቶች ፍላጎት ያጠናል፤

❖ በጥናትና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ለክልሉ ልማት ኃይሎች ከሥራ አመራር ጋር የተያያዙ የአጭርና መካከለኛ ጊዜ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

❖ በተቋሙ የሚሰጡ የሥልጠና፣የምርምርና የምክር አገልግሎቶች ምን ያህል ተጨባጭ ለዉጥ ሊያመጡ እንደቻሉ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት በየጊዜዉ ያካሂዳል፤

❖ በሀገሪቱ በተለይም በክልሉ የሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት፣ስልጠና ጥናትና ምርምር ተቋማት ጋር በመደጋገፍና በመቀናጀት ይሰራል፤

❖ የስልጠናና የጥናት ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት እንዲሁም የምክር አገልግሎቶችን በመስጠት ከተለያዩ ምንጮች ገቢ የሚያገኝበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

❖ ለሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፣ዝርዝር አፈፃፀሙ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወሰን ሆኖ የሰበሰበዉን ገቢም ለስልጠና፣ለምርምርና ለምክር አገልግሎቶች ማስፋፍያ ይጠቀማል፤ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ዉል ይዋዋላል፣ይከሳል፣ይከሰሳል የሚሉ ስልጣንና ተግባራትን ይዞ የተቋቋም

ተቋም ነዉ፡፡

**ቦርዱ ከምስረታ ዘመኑ ጀምሮ እስካሁን ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት፣**

ተቋሙ በ1991 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 15/1991 መጀመሪያ ሲቋቋም በቦርድ እንዲተዳደር ወይም እንደሚመራ በአዋጁ የተገለፀ ቢሆንም የቦርዱ ሰብሳቢ እና አባላት በስራ አስፈፃሚ ይሰየማሉ፣ አባላቱም ተጠሪነታቸው ለክልሉ መንግስት ርዕሰ-መስተዳደር እና ለስራ አስፈፃሚ ኮሜቴው ነበር። ስለዚህ በወረቀት ላይ ከሰፈረው ስም አልፎ በተጨባጭ ወይንም በአካል የሚመራ ቦርድ የተቋቋመ ስላልነበረ ሁኔታው ለተቋሙ መዳከም ተጨማሪ ችግር ሆኖ ቆይቷል። ቦርዱ ሲቋቋም የቦርዱ እና የተቋሙ ሥልጣን እና ኃላፊነት በተዋረድ በአዋጅ ቢጠቀስም ቦርዱ በአካል ስላልተመሰረተ በተቋሙ ስራዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲያሳድረ ቆይቶል። ተቋሙ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ መወጣት እንዲችል እና የነበሩበትን ችግሮች መቅርፍ የሚያስችለውን በ2002 ዓ.ም ተቋሙ እንደገና እንዲሻሻል እና እንዲደራጀ ሲደረግ ተቋሙ በቦርድ እንዲተዳደር ተደርጓል። በ17/08/2003 ዓ/ም ቦርዱ የመጀመሪያ ስብሰባውን ሲያካሂድም ሆነ ከዚያ በኃላ የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፋል። ከነዚህም መካከል፡-

የተቋሙ አሰልጣኞች ፣አማካሪዎች እና ተመራማሪዎች መተዳደሪያ መመሪያ ተወይቶ አፀድቆል፣ የተቋሙን የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣አጠቃቀም፣ሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራሪብ ረቂቅ ደንብ መርምሮ ለካቢኒ በማቅረብ እንዲጸድቅ አድረጓል፣

 የተቋሙ በውጤት ተኮር ስርዓት የተቃኘ የGTP I ፤ የGTP II እና የGTP III ዕቅድ እና ሪፖርት አፈጻጸም በመገምገም እና በማጽደቅ እንዲሁም ተቋሙ በውጤት ተኮር ስርዓት እንዲመራ በተቋሙ የተዘጋጀውን የአፈጻጸም እና የትግበራ መመሪያ መርምሮ የስራ መሳርያ እንዲሆን አድርጓል፣

 ተቋሙ የሰው ሀይል እንዲሟላ በተለይም በአላማ አስፈጻሚ የተሻሉ አሰልጣኞች፤ተመራማሪዎች እና አሰልጣኞች ወደ ተቋሙ እንዲገቡ የተለያዩ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፣

 የተቋሙ የቦርድ አሰራርና የአሰራር ሰነ-ስርዓት መመሪያ ተወያይቶ አፅድቆ የስራ መሳርያ እንዲሆን አድረጓል፣

 የተቋሙን የስልጠና በጀት አጠቃቀም እየመረመረ የመፈትሄ አቅጣጫ እያስቀመጠ ይገኛል፣

 የተለያዩ የተቋሙ መመሪያዎች እና ደንቦችን ተወይቶ አፀድቆል፣ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የስራ አመራር ቦርዱ አልፎ አልፎ ወቅቱን የጠበቀ

ስብባዎችን አለማድረግ፣ ተቋሙ ለክልሉ አመራርና ፈፃሚ ሀይል የተሟላ ስልጠና በመስጠት ደርሻዉን እንዲወጣ የሚስችል አደረጃጀትና አሠራር እንዲኖር ክፍተቶች መታየታቸው፣ የሌሎች ክልሎች ሥራ አመራር ተቋማት የስራ አመራር ቦርድ ተሞክሮ በመዉሰድ ወደ ተቋሙ በመቀየር ተግባራዊ አለማድረግ በክልሉ በሚገኙ ሴ/መ/ቤቶች የለዉጥ ፕሮግራሞች በአግባቡ እንዲመሩ አለማድረግ ዉስንነት ይታይበታል፡፡

**ተቋሙ በምስረታ ዘመኑ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የነበረው የስራ ግንኙነት፣**

ተቋሙ በምስረታ ዘመኑ የሰዉ ሀይል፣ የቁሳቁስ እና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጉለት ለጋሽ ድርጅቶች UNDP፣ CIDA CLADA፣ VSO Ethipia እና DSA/Decentralized Support Activity/ሲሆኑ ለተቋሙ ያደርጉት ድጋፍ ጥቂቱን በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**1.3.1. ከተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት/UNDP/፣**

ተቋሙ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በተመረጡ የፖይለት ወረዳዎች ማለትም በመንጌ እና በሎጅጋንፎይ ወረዳ ከUNDP በተገኘው የበጀት ድጋፍ፤

❖ በተለያዩ የስልጠና ርእሶች ከላይ ከተመረጡ ወረዳዎች እና የክልል ሴ/መ/ቤቶች የሚገኙ አመራሮች እና ባለሙያዎች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ተደረጓል፤

❖ የምዕተ አመቱ የልማት ግቦች ለማሳካት በተቋሙ ውስጥ Millennium-Development Goal Knowledge center /MDGKC/ ኘሮጀክት ተቀርጾ የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን 12 ኮምፖተሮችን ፣እስካነር፣ፎቶ ኮፒ እና የተለያዩ ማጣቀሻ መጽሀፎችን እርዳታ አድርጓል፡፡ ለስልጠና አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁስ ግዥ እንዲፈጸም የተደረገ ሲሆን ከነዚህም መካከል /አንሶላ፣አልጋ፣LCD projector እና የምግብ ቁሳቁሶች ናቸው፡፡

❖ ለፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ አንድ ሎንግ ቤዝ መኪና በእርዳታ ለተቋሙ መሰጠቱ፡፡

**1.3.2 ሲዳ ካናዳ /CIDA CANADA/**

 ለኢንተርኔት ካፌ ተጠቃሚዎች ሰርቪስ አገልግሎት የሚውል አንድ ኮስተር መኪና ግዥ በመፈፀም ለተቋሙ ተሰጥቷል፡፡

 ለተቋሙ አገልግሎት የሚውሉ ወንበር እና ጠረጴዛ እርዳታ አድርጓል፣ የተቋሙን የ10 ዓመታት ስልታዊ ዕቅድ/SPM/ በአማካሪ ድርጅት እንዲጠና አድረጓል፣ ባጠቃላይ ተቋሙ በምስረታ ዘመኑ ያሉበትን ችግሮች በመቋቋም አሁን ለሚገኝበት ደረጃ መሰረት የጣለ ነበር፡፡ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት ተቋሙ በምስረታ ዘመኑ አካባቢ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የነበረው መልካም የስራ ግንኙነትና መደጋገፍ

እንደተጠበቀ ሆኖ በወቅቱ ተቋሙን ይመሩ በነበሩ አመራሮች ከላይ የነበሩት ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ተነጥቀዉ ለክልሉ አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ከመዞራቸዉም በላይ ተቋሙ ከራሱ የዉስጥ ገቢ የተገዛና በUNDP እርዳታ የተሰጠ መኪናዎችም ( ማለትም አንድ ሎንግ ቤዝና አንድ ኮቢራ መኪና) ወደ በወቅቱ የክልሉ አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ተብሎ በሚጠራው ቢሮ እንዲዘዋወሩ ተደረዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በወቅቱ በሚገባ ከክልሉ መንግስትም ለተቋሙ ትኩረት ያልተሰጠዉ በመሆኑ ተቋሙ መስጠት የሚገባዉን አገልግሎት ለረጅም ጊዜያት እንዳይሰጥ ከፈተኛ ተጽእኖ አድርሶበታል፡፡